የመ/ቁ.16378

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ቀረበ

ተጠሪ፡- በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቅ/መ/ቤት ነገረፈጅ አቶ ፈርተውሃል ኃይለጊዮርጊስ ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ መውሰድ ይችላል አይችልም፣ ሁለቱን በጣምራ ወስ ከተገኘ የጡረታ አበሉን ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ሲወስድ የቆየ መሆኑ ቢረጋገጥም ደመወዙንም ሆነ የጡረታ አበሉን የሚመልስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የወሰነውን የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.348(1) መሠረት



በመሻር ቀደም ሲል በሥራ ላይ በቆየው የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30/2/ መሠረትም ሆነ በኋላ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 46/1/ መሠረት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝ ማግኘት ከጀመረ የጡረታ አበል እና ደመወዝ በጣምራ ሊወሰድ አይችልም፣ በሕጉ የጡረታ አበሉ ተቋርጦ ይቆያል፣ ስለዚህ 10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ ይገባዋል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ያለአግባብ ሲቀበል ቆይቷል የተባለው የጡረታ አበል በአጠቃላይ ብር 9000 ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም እንዲመልስ የወሰነው ይህንኑ ገንዘብ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡ አመልካች ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ አለበት በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ነው ለሰበር አቤቱታ ያቀረበው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲደርሰው ተደርጐ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በጽሑፍ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አንድ የጡረታ መብቱ የተከበረለት ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ከተቀጠረ የጡረታ ሕጉ የጡረታ አበሉ ወዲያውኑ የሚቋረጥ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንደተቀጠረ ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ ሲገባው ደብቆ ደመወዝና የጡረታ አበል ያለአግባብ በጣምራ ሲቀበል ቆይቷል፡፡ መሥሪያ ቤቱ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መ/ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መቀጠሩን የሚያውቅበት መንገድ ስለሌለ የጡረታ አበሉን እንዲያቋርጥ ለማድረግ አይችልም፡፡ የጡረታ አበሉን ሲከፍለው የቆየው ደመወዝ ማግኘቱን እያወቀ አይደለም፡፡ አመልካች በሕግ የጡረታ አበል ስለመቋረጡ አላውቅም የሚለው መከላከያ

መልስ ሊሆነው አይችልም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሣኔም የተፈፀመ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ሊቀጠር ከቻለ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሊቀበል ይችላል አይችልም፤ የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ከደመወዝ ጉን ለጉን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰራ ከቆየበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከታህሣሥ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለል ተደርጉ የተወሰነለትን የጡረታ አበል ማግኘት ከጀመረ በኋላ ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዝ በሚያስገኝ ሌላ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በመሥራት ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ተከሣሹ የአሁኑ አመልካች ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየው ያለአግባብ ስለሆነ የጡረታ አበሉን ሊመልስ ይገባል በሚል የከሰሰው በታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም ነው፡፡ ይኼው ከተረጋገጠ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆነው በኋላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 ሣይሆን በወቅቱ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ በሥራ ላይ የነበረው ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና ይህንኑ ድንጋጌ በከፊል በማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 209/55 ነው የተጠቀሰው ድንጋጌ አንቀጽ 30/2/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደመወዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ አለበት ይላል፡፡ ከዚህ ሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ መብት የተሰጠው ለሠራተኛው ነው፡፡ በሕግ ከተፈቀደለት የጡረታ አበል እና ተመልሶ ከተቀጠረበት የመንግሥት ሥራ ከሚያገኘው ደመወዝ የበለጠ ይጠቅመኛል የሚለውን የመምረጥ እድል በሕጉ ስለተሰጠው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ እንደተቀጠረ በአካባቢው ላለው የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ ምርጫው ምን እንደሆነ መግለጽ ይኖርበታል፡፡ የበለጠ የሚጠቅመኝ አዲሱ ደመወዝ ነው ካለ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ በሚቀጠርበት ጊዜ ራሱ ወይም ቀጣሪው መሥሪያ ቤት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካላሣወቀ በቀር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚያውቅበት



መንገድ ስለሌለ ተከታትሎ የጡረታ አበሉን ማቋረጥ ነበረበት የሚለው ከጡረታ ሕጉ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት የለውም፡፡

ጡረታ የወጣው ሰው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ አዲስ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕጉ ምን ይደረጋል? የሚለው ሲመረመር ሕጉ ደመወዙን ወይም የጡረታ አበሉን ይመልሣል የሚል ግልጽ ድንጋጌ ባይኖረውም በሕጉ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም ከተባለ አጣምሮ ሲቀበል የቆየውን በሕግ ያልተፈቀደለትን ገንዘብ የማይመልስበት ምክንያት የለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች ከደመወዝ ጎን ለጉን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል እንዲመልስ ጠይቋል፡፡ ሆኖም አመልካች በወቅቱ በሕጉ በተሰጠው ከአዲሱ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አንዱን የመምረጥ መብት ስላልተጠቀመ ሊመልስ የሚገባው ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን ገንዘብ ነው፡፡ በሕጉ ላይ በተገለፀው መሠረት ሊመርጥ ቢችል ኖሮ ከሁለቱ ከፍ ያለውን ገንዘብ ይመርጣል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከተቀጠረበት ሥራ የሚያገኘው ደመወዝ ዝቅተኛ ሆኖ የጡረታ አበሉ ከፍተኛ ከሆነ የጡረታ አበሉን ትቶ ዝቅተኛ የሆነውን ደመወዝ ይመርጣል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ፍትሐዊም የሚሆነው አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል መካከል ዝቅተኛ የሆነውን እንዲመልስ ማድረግ ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝ እና የጡረታ አበል መካከል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን እንዲመልስ ወይም ለተጠሪው እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡